# መ-1

# የብሄራዊ ድርጅቶች፤ የአዲስ አበባ፤ የድሬዳዋ፤ የዞንና የክፍል ከተማ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር፣ አደረጃጀትና አሰራር የፀደቀ መመሪያ

ሰኔ 2002

<u>አዲስ አበባ፤</u>

# መ ግ ቢ ያ

የብሄራዊ ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ የወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አደረጃጀት እና አሰራር እንዲሁም ተግባር እና ሃላፊነት በየራሳቸው መስራች ጉባኤ ላይ በፀደቀው መተዳደሪያ ደንብ ላይ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም መተዳደሪያ ደንቡ የጽ/ቤቱ ሃላፊነት እና ተግባር እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ የተጠሪነት ጉዳዮችንም በዝርዝር ወስኗል፡፡

በዚሁ መሰረት የወጣት ሊጎቹ በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ የተቀመጡ አደረጃጀቶች እና የአሰራር መመሪያዎች እንዳሉ በመውሰድ መተዳደሪያ ደንቡ ለጽ/ቤቱ የሰጣቸውን ተግባራት እና ሃላፊነት በብቃት ለመፈፀም የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የአደረጃጀት እና የአሰራር አግባብ የተሻለ አማራጭ መሆኑ ታምኖበት ተግባራዊ እንዲሆን ቀርቧል፡፡

## ክፍል አንድ

## 1. የክልል እና የከተማ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮ እና አሰራር፤

**ሀ. የብሄራዊ ድርጅቶች፣የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ ወጣቶች ሊግ ስራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፤**

- የብሄራዊ ድርጅት፣የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡
    1. የጽ/ቤት ኃላፊ፤
    2. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ፤
    3. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ፤
    4. የሱፐርቪዥን ዘርፍ ኃላፊ እና
    5. የስልጠና ዘርፍ ኃላፊ ናቸው፡፡

**ለ. የብሄራዊ ድርጅት፣ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተልዕኮ፤**

1. የብሄራዊ ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት በመተዳደሪያው ደንቡ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የክልሉ እና የከተማው ፖለቲካ እና ድርጅታዊ ስራ ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ፤
2. ከኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክልል/ከተማ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካ እና የድርጅት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን በስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል፣ በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፤
3. በየደረጃው ያለው የድርጅት አደረጃጀት አመራር አባላት፣ በስራቸው ግንባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸውን ማዳበር፤
4. በክልሉ/በከተማው የሚካሄደውን ልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካ እና የድርጅታዊ ስራዎችን ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን በመለየት እና በመቀመር በመላ ክልሉ/ከተማው እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

5. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራው በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑ እና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራውን እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የህዋስ እና የመሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራችንን ያቅዳል፣ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

6. በሊጉ የሚካሄደውን የአባላት እና የአመራር ስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፤

7. የሊጉ የአሰራር እና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፤

8. የሊጉ አባላት ማህደር እና ሰነዶች በአግባቡ መደራጀታቸውን እና መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

9. የሊጉን አመራር የስነ ምግባር እና የመፈፀም ብቃት በማዳበር የአባላቱን የተደራጀ አህዳዊ እንቅስቃሴ የሚመሩ አመራር መፍጠር፤

10. የሊጉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች የተለያዩ የሊጉን ክፍል ተልዕኮ በመከፋፈል ስራውን በጋራ የሚመሩበተ ሁኔታ መፍጠር፡፡

ሐ. የብሄራዊ ድርጅቶች፣ **የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ** ከተማ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር አሰራር፤

1. የብሔራዊ ድርጅት ወ□ቶች ሊግ ስራ አመራር ኮሚቴ እንቅስቃሴውን የሚመራበት አመታዊ ዕቅድ ይኖረዋል፡፡ የመነሻ ዕቅድ ከኢህአዴግ ወ□ቶች ሊግ በሚሰጥ አቅጣጫና በብሔራዊ ድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ በፀደቀው ዕቅድ መነሻ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤
2. የአመቱን ዕቅድ መነሻ በማድረግ በየሩብ አመቱ በመዘርዘር ለፈፃሚ አካላት ተገቢውን አሬንቴሽን ይሰጣል፤
3. ለቁጥጥርና ክትትል በሚያመች መልኩ ቼክ-ሊስት አዘጋጅቶ ዕቅዱ በጥብቅ ድስፕሊን መፈፀሙን ያረጋግጣል፤
4. በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ የአፈፃፀም ችግሮች ሲኖሩ አስፈላጊውን ማስተካከያና ድጋፍ ይሰጣል፤

5. ሳምንታዊ መደበኛ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ በሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል፤
6. የዞንና የወረዳ የሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡-
   - በየሩብ አመቱ ከዞን ወ□ቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፣
   - በየወሩ ዞኖች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ የፅሑፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ-መልስና ድጋፍ ይሰጣል፣
   - በየሳምንቱ ከዞኖች ጋር የስልክ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል፣
   - አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት ዕቅድ ለዞን /ለወረዳ/ ወ□ቶች ሊግ አመራር ኦሬንቴሽን ይሰጣል፣
7. በልሳናትና በራሪ ጽሑፎች፣ በጋዜጣ እንዲሁም በመጽሔት ለሚካሄደው የሊግ ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፣
8. በየ3ወሩ በክልሉ ካሉት ዞኖችና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን በየ6 ወሩ ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል:: ናሙናው የሚመረጠው ጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ የተባሉትን በመምረጥ የሚፈፀም ይሆናል፣
9. የጽ/ቤቱን በጀት በማዘጋጀት ለሊጉ ስራ አስፈፃሚ በማቅረብ ማዕከላዊ ኮሚቴ በስራ ላይ እንዲያውል ያደርጋል፣
10. ለኢህአዴግ ወ□ቶች ሊግ ጽ/ቤት በ2 ሳምንት የስራ ኢንፎርሜሽን መስጠት፣ በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፣
11. ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ድርጅት ወ□ቶች ሊግ ሊቀመንበር እና ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል::

1. የጽ/ቤት ኃላፊ ተግባር እና ኃላፊነት፤

   1.1. የሊጉ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሊጉ ሊቀመንበር እና በስራ አስፈጻሚ ይሆናል:: ሆኖም ሊቀመንበሩ የጽ/ቤት ኃላፊ በሚሆንበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ይሆናል፤

1.2. የሊጉን ጽ/ቤት የህዝብ ግንኙነት እና የአደረጃጀት እንዲሁም የፋይናንስ እና የሰው ሃይል አስተዳደር ስራዎች ያስተባብራል፣ ይመራል፤

1.3. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና ከሊቀመንበሩ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ይፈፅማል፣

1.4. የጽ/ቤቱን በጀትና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣

1.5. ስለ ጽ/ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ ለሊቀመንበሩ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

1.6. የሊጉን ጽ/ቤት በመወከል ውል ይዋዋላል፣

1.7. በሊጉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ ላይ በመመስረት ከዞን፣ ከክፍለ ከተማ እና ከወረዳ አመራሮች ጋር እየተገናኘ አጠቃላይ በክልላዊ እና ሃገራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል።

## 2. የፖለቲካ ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት፤

- የፖለቲካ ዘርፍ የሚከተሉትን ዋና ዋና ስራዎች እና ኃላፊነት ይኖሩታል፣ እነዚህ የአባላት ፖለቲካዊ ግንባታ፣የህትመት እና የሚዲያ ስራዎች ናቸው።ዝርዝር ተግባሮች እና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው።

2.1 የአባላት ፖለቲካዊ ግንባታ፤

2.1.1. በስልጠና አማካኝነት የሚደረግ ፖለቲካዊ ግንባታ፤

2.1.2. የስልጠና ፍላጎት ማጥናት፤

2.1.3. የስልጠናውን ውጤት በመገምገም ተሞክሮ መቀመር፤ የስልጠናውን አፈፃፀም በሚመለከት ለሁሉም የወጣቶች ሊግ መዋቅሮች ሪፖርት መላክ፤

2.1.4. የአባላት የስልጠና አቅም መደገፍ፣በየደረጃው ከሚገኙ መዋቅሮቻችን ያሉ ተሞክሮዎችን መቀመር እና ማስፋፋት፡፡

2.2 የዕለት ተዕለት ፖለቲካ ግንባታ፤

2.2.1 የጋራ አመለካከት መፍጠር የሚያስችል አጀንዳዎችን መወሰን እና መልዕክት መቅረፅ፣

2.2.2 በተቀረፁ ፖለቲካዊ አጀንዳዎች እና መልዕክቶች ዙሪያ በየደረጃው ያሉ አመራሮች እና አባላት ሁሌም የተሟላ ግልፅነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣

2.2.3 የሊጉ አባላት ወጥ የሆነ ፖለቲካዊ አመለካከት እንዲኖር የሚያደርጉ ስራዎችን ማቀድ፣የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን ማዘጋጀት፣አፈፃፀሙን ተከታትሎ ማረጋገጥ፣

2.2.4 የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራው ለዚሁ ስራ ተብሎ በተቀመጡ የአደረጃጀት እና የአሰራር መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን ማረጋገጥ፣

2.2.5 በአጫጭር ስልጠና እና የዕለት ተዕለት ግንባታ አማካኝነት ለተልዕኮ ብቁ የሆነ ፖለቲካዊ ግንዛቤ እና አቋም ያለው የህዋስ እና መሰረታዊ ድርጅት መፍጠር፣

2.2.6 የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራ አፈፃፀም በተመለከተ ጠንካራ የሪፖርት እና የግብረ-መልስ ስርአት መዘርጋት እና ተግባር ላይ መሆኑን ማረጋገጥ፣

2.2.7 የዕለት ተዕለት ግንባታው ትግበራው የልማት እና የመልካም አስተዳደር አፈፃፀሞች ላይ እያመጣ ያለውን ተፅዕኖ በቀጣይነት ማጥናት እና በቀጣይ የዕለት ተዕለት ግንባታ እንቅስቃሴ በግብአትነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ።

2.3 የሚዲያ ስራዎች፤

- በዚህ ግንባታ መስክ ስር የሚካተቱ የአባላት ግንባታ መሳሪያዎችን፣ወቅታዊ ፅሁፎችን፣የኮንፈረንስ ፅሁፎችን እና ሌሎች የሚዲያ ስራዎች ናቸው።

2.3.1 የወቅታዊ ፅሁፎች ዝግጅት ስራ በተመለከተ፡-

- የመድረኩ አስፈላጊነት እየታዩ የሚዘጋጁ ወቅታዊ ፅሁፎች ይኖራሉ፣

2.3.2 በየደረጃው ከሚገኙ የሊጎች ጽ/ቤቶች ጋር ጠንካራ የስራ መደጋገፍ እና የቅንጅት ስራ እንዲኖር ማድረግ፣

2.3.3. በብሄራዊ ድርጅቶች የሚወጡትን ጋዜጦች መጠቀም፣

2.3.4 ተጠሪነቱ ለጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።

## 3. የሊጉ የድርጅት ዘርፍ ተግባር እና ኃላፊነቶች፤

- የብሄራዊ ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ወጣቶች ሊግ የድርጅት ዘርፍ በዋናነት የውስጠ ድርጅት ስራዎች፣ የደጋፊ አደረጃጀቶች ማጠናከር እና የመገንባት ስራ እንዲሁም የዶክመንቴሽን ስራዎች ናቸው፡፡ ዝርዝር ተግባሮች እና ኃላፊነቶች፤

### 3.1 የውስጠ ድርጅት (ሊግ) ስራዎች፤

3.1.1 አቅም ያለውና በጥሩ ስነምግባር የታነፀ አመራር መፍጠር እና ማጠናከር፣

3.1.2 በሁሉም የሊጉ መሰረታዊ ድርጅቶች እና በሁሉም ህዋሳት ደረጃ ያለው አመራር በልማት ስራ ውጤት ግንባር ቀደም የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ፤

3.1.3 የሊጉ መካከለኛ አመራር ጠንካራ የበላይ አመራር ምንጭ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የታቀዱ የግንባታ ስራዎችን መስራት፣

3.1.4 ሁሉም የሊግ አባላት በተሰማሩባቸው የስራ መስኮች ግንባር ቀደም እንዲሆኑ እና ደጋፊዎችን በዙሪያቸው የሚያሰባስቡ አባላት መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

3.1.5 ጠንካራ የሊጉን መዋቅር በመፍጠር የአባላት ቁጥራችንን በእጅጉ ማስፋት የልማት እና መልካም አስተዳደር እንቅስቃሴ ውስጥ በተግባር እንቅስቃሴ እና በስራ ውጤቱ ተለክቶ እየተገነባ የሚሄድበትን የአሰራር አግባቦች መቀየስ እና ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ፣

3.1.6 የአባላትን ፖለቲካዊ ጤንነት በቀጣይነት ማረጋገጥ፤

3.1.7 የአደረጃጀት እና የአሰራር መመሪያዎችን በቀጣይነት መፈተሽ ከወቅቱ የትግል መድረክ ጋር የማይሄዱትን ማስወገድ፣መቀጠል የሚገባቸውን ማስቀጠል፣ አስፈላጊነታቸው የታመነባቸው አዳዲስ አሰራሮችን መቀየስ እና መተግበር፣

3.1.8 በየስድስት ወሩ እና በአመት አንድ ጊዜ በመደበኛነት እያንዳንዱ አባል እና አመራር በተግባራዊ እንቅስቃሴ እና ተልዕኮዎቹን ከመወጣት አኳያ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ የሚያሳይ የግለሂስ መደበኛ ሪፖርት አዘጋጅቶ ማቅረብ፣

3.1.9 ከላይ በተጠቀሱ የጊዜ ገደቦች ውስጥ እና የዕቅድ አፈፃፀም ምዕራፎች ውስጥ የሚደረጉ የስራ ግምገማዎች እና ሂስ ግለ ሂሶች ወቅታዊነታቸውን ጠብቀው መካሄዳቸውን ማረጋገጥ፣ግምገማዎቹን መነሻ በማድረግ፣ እያንዳንዱ አባልና አመራር በስራ ውጤቱ ተለክቶ እንደሁኔታው የሚሸለምበት፣የሚቀጣበት ወይም የሚሸጋገርበት አሰራር በተግባር አዘጋጅቶ ስልጣን ላለው የበላይ አካል ማቅረብ፣ በአመራሩ ሲፀድቅ በሁሉም የሊጉ መዋቅሮች አማካኝነት የተሸለሙ፣የተቀጡ እና የተሸጋሸጉ አባላትን ማንነት እና ወይም መጠን ከበቂ ማብራሪያ ጋር በጽ/ቤቱ በመረጃነት ተመዝግቦ እንድቀመጥ ማድረግ፣ ስለዚሁ ጉዳይ መደበኛ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጽ/ቤቱ የስራ አመራር ኮሚቴ ማቅረብ፣

3.1.10 በሊጉ ውስጥ በየደረጃው ባለው አደረጃጀት አንድም ያልታቀፈ አባል እንዳይኖር በማረጋገጥ ተልዕኮ ያልተሰጠው አባል እንዳይኖር ብቻ ሳይሆን በተልዕኮው ያለተመዘነ አንድም አባል የማይኖርበት ሁኔታ በሊጉ ውስጥ እንዲሰፍን በማድረግ መላው አባላችን በተለይም የገጠር አባላችን አሁን ከተበተነ እና ካልተጠናከረ ሃይልነት ወደ ተደራጀ በፖለቲካ አቅሙ ጠንካራ ሃይልነት እንዲሸጋገር ማድረግ።

## 3.2 የወጣት ማህበራት አደረጃጀትን በተመለከተ፤

- በዚህ ዙሪያ የሚነሱ የተለያዩ ሙያዎች ፆታንና ዕድሜን እንዲሁም የስራ መስኮችን ማዕከል አድርገው የተደራጁ እና የተለያዩ ቁጥር ያሏቸው አባላትን በዙሪያቸው ያሰባሰቡ ማህበራትና አደረጃጀቶች ናቸው፤
- እነዚህ የተቋቋሙበት የራሳቸው አላማ እና ፕሮግራሞች እንዲሁም የሚመሩባቸው ውስጠ ደንቦች ያሏቸው መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ የሚከተሉትን ስራዎች እንሰራለን፤

3.2.1 በወጣቶች ማህበራት ውስጥ የሊጉ አባላትን በስፋት ማፍራት እና ማጠናከር በስራ ትጋታቸው እና በስነ ምግባራቸው ምሳሌ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን የፖለቲካ እና የአደረጃጀት ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣

3.2.2 በአጠቃላይ ህጋዊ እና ዴሞክራሲያዊ ከሆነ ማናቸውም የወጣቶች ማህበራት በትብብርና በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ግንኙነት መመስረት እና ማጠናከር፣

3.2.3 የወጣቶች ማህበራት በመካከላቸው ያለው ግንኙነት እንዲጎብር ለማድረግ በወጣቶች ፌዴሬሽን ስር ተሰባስበው የሚያደርጉትን ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት፣

3.2.4 የወጣቶች ማህበራት በየመስኮቻቸው ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤት አመራር አካላት ጋር ተገናኝተው አስፈላጊውን ድጋፍ እያገኙ እና እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ሁኔታ ማመቻቸት።

3.3 የዩኒቨርሲቲ አደረጃጀትን በተመለከተ፤

3.3.1 እናት ፓርቲያችን በዩኒቨርሲቲዎቻችን ውስጥ የአባላት አደረጃጀት መመሪያን ባስቀመጠበት አቅጣጫ በማጣጣም የሚሰራ ሆኖ ስራው እና አደረጃጀቱ በተሟላ መንገድ እንዲካሄድ ሊጉ በተቀናጀ መልክ የሚንቀሳቀስ ይሆናል።

3.4 የዶክመንቴሽን ስራን በተመለከተ፤

3.4.1 የሊጉ መሰረታዊ ሰነዶች የድምፅ የምስል እና የፅሁፍ በጥንቃቄ እና በዘመናዊ መንገድ እንዲያዙ ማድረግ፣

3.4.2 የሊጉ ምክር ቤት እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሁም የቃለ ጉባኤ ሪፖርቶች እና ቃለ-ጉባኤዎች በአግባቡ እንዲያዙ ማድረግ፣

3.4.3 በየአመቱ ስራ ላይ የዋሉ እቅዶች፣ፕሮግራሞች ከተለያዩ አካላት ጋር የተደረጉ ግንኙነቶችን በሰነድነት እንዲያዙ ማድረግ።

3.5 የፋይናስ እና የሰው ሃይል አስተዳደርን በተመለከተ፤

- የብሔራዊ ድርጅቶችና አዲስ አበባ እንዲሁም ድሬዳዋ የፋይናንስና የሰው ሃይልን በተመለከተ ራሱን ችሎ የፋይናንስና የሰው ሃይል መመሪያ የሚወጣ ይሆናል።

3.6 ተጠሪነቱ ለጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## 4. የሱፐርቪዥን ስራን በተመለከተ፤

- የሱፐርቪዥን ስራ ራሱን በቻለ ዘርፍ የሚደራጅ ሆኖ የሚከተሉት ሃላፊዎች ይኖሩታል፡፡

4.1. በየደረጃው ያሉ አባላት፣ የአመራር አካላት፣አደረጃጀቶችና ተግባሮቻችን ያሉበትን ተጨባጭ ሁኔታ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸው ምን እንደሚመስል የሚያሳዩ ጥናቶችን በቀጣይነት እና በየወቅቱ በማወቅ የተደራጀና ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለጽ/ቤቱ ማቅረብ፣

4.2. የገጠሩን እና የከተማ የወጣት ሊግ አባላት ሁኔታና ሌሎች የወጣት አደረጃጀቶች ሁኔታ በማጥናት ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ሪፖረት ለጽ/ቤቱ ማቅረብ፣

4.3. የተቃዋሚ - ርቲዎች ሁኔታዎችን በየጊዜው በወጣቶች አደረጃጀት ውስጥ መከታተል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከእናት ፓርቲያችን ጋር ጉዳዩን እየተወያዩ መፍትሄ ማስቀመጥ፣

4.4. ጠንካራ የሱፐርቪዥን ክፍል በሊጉ ጽ/ቤት ደረጃ ከመገንባት ጎን ለጎን በዞን/ክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ ተመሳሳይ አቅም እንዲፈጥሩ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

4.5 ተጠሪነቱ ለጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## 5. የስልጠና ዘርፍ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት፤

1. የሊጉን ፖለቲካዊ እና ድርጅታዊ ስራዎች በጥናት እና ምርምር መደገፍ
2. አጠቃላይ የስልጠና ዕቅድን መምራት እና ከፖለቲካ ዘርፍ ጋር በተቀናጀ መልኩ በየጊዜው የሚሰጡ ስልጠናዎች ያመጧቸውን ለውጦች በመገምገም ቀጣይ አቅጣጫ መቀየስ፤
3. በተጨማሪ ከጽ/ቤቱ የሚሰጡትን ስራዎች ይሰራል፤
4. ተጠሪነቱ ለፅ/ቤቱ ሃላፊ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የዞን እና የክፍለ ከተማ አደረጃጀት ተልዕኮ እና አሰራር፤

- የዞን እና የክፍለ ከተማ አመራር ከክልሉ የሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴ ወይም ከዚያ ውጭ ጠንካራ አባል ሁለት ሰው ተመድቦ ፖለቲካዊ እና ድርጅታዊ ስራዎችን የሚሰራ ሲሆን የሚከተሉትን ተልዕኮ ይኖሩታል፣

1. ከብሔራዊ ድርጅት (ክልል) ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ የዞን፣ የክፍለ ከተማ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካ እና የድርጅት ስራዎችን ያቅዳል፡፡ ፈፃሚውን አካል ኦሬንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፤
2. የዞን እና የክፍለ ከተማ ጽ/ቤት የዞን እና የክፍለ ከተማ የፖለቲካና ድርጅታዊ ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤
3. በየደረጃው የሚገኙ የሊጉ አመራሮች ግንባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸውን ማዳበር፤
4. በዞኑ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካ እና ድርጅታዊ ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን በዞኑ እና በክፍለ ከተማ እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
5. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑን እና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራውን እያጠናከረ ይሄዳል፤
6. ጠንካራ የሊጉ ህዋስ እና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራችንን ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይመራል፤
7. በዞኑ እና በክፍለ ከተማ የሚካሄደውን የአባላት እና የአመራር ስልጠና፣ ሴሚናር የመሰረታዊ ድርጅቶች ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

8. የሊጉ የአሰራር እና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች በዞኑ እና በክፍለ ከተማ በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፤

9. ስለ መመሪያው ተግባራዊነት በየጊዜው ተከታትሎ ራሱን የቻለ ሪፖርት ያቀርባል፤

10. በዞን እና በክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የአባላት ማህደር፣ የሊጉን ሰነዶች በአግባቡ መደራጀታቸውን እና መያዛቸውን ማረጋገጥ፤

11. በዞኑ እና በክፍለ ከተማ የሚከናወኑ የፖለቲካ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

12. ሊጋችንን በአዳዲስ ግንባር ቀደም ሃይሎች የሚያጎለብትበትን ሁኔታ በዞኑ፣ በክፍለ ከተማ ውስጥ የማስፋት ስትራቴጂውን ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

13. በዞኑ እና በክፍለ ከተማው በየደረጃው ያሉትን የወረዳ እና የቀበሌ ሊግ መዋቅር ፖለቲካዊ ብቃት የመገንባት፣ ጠንካራ የልማት እና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ስትራቴጂ መሰረት እየመሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ድጋፍ መስጠት፤

14. የዞኑ እና የክፍለ ከተማውን ሊግ አባላት ዴሞክራሰያዊ አስተሳሰብ አዳብሮ በዚያም እየተመራ ልማታዊ እና ዴሞክራሲያዊ ተግባራቱን በማጎልበት ተጠቃሚነቱን እያሰፋ እና በዞኑ፣ በክፍለ ከተማ የሚገኙ የሊጉ አመራር ተልዕኮውን በብቃት ለመወጣት በሚያስችል ሁኔታ ኮሚቴው በቀጣይነት ራሱን ማብቃት ይኖርበታል፤

15. በዞኑ እና በክፍለ ከተማ ውስጥ በፖለቲካ ንቅናቄ ሊመሩ የሚገባቸው ተግባሮች በመለየት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፣ አስፈፃሚ ሃይሎችን ያዘጋጃል፣ የወጣቱ ንቅናቄ ስራ መሆኑን ተረድተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤

16. የዞኑን እና የክፍለ ከተማውን ወጣቶች ሊግ አመራሮች የተናጠል ተግባር እና ሃላፊነት እንዲሁም አሰራር በተመለከተ ከሊጉ አደረጃጀት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የየብሄራዊ ድርጅቱ ወጣት ሊግ አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ ጽ/ቤት አዘጋጅቶ እንዲሰጥ ይደረጋል።

**ለ/ የዞን /ክፍለ ከተማ/ ወ□ቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ አሰራር፤**

1. የዞኑ ሊግ ስራ አመራር ኮሚቴ እንቅስቃሴውን የሚመራበት አመታዊ ዕቅድ ይኖረዋል። የዕቅዱም መነሻ ከብሔራዊ ድርጅት ሊግ በሚሰጥ አቅጣጫ መሰረት የዞኑን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ በፀደቀው ዕቅድ መነሻ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፤
2. የዞኑን አመታዊ ዕቅድ መነሻ በማድረግ በየሩብ አመቱ በመዘርዘር ለፈፃሚ አካላት ተገቢውን ኦሬንቴሽን ይሰጣል፤
3. ለቁጥጥርና ክትትል በሚያመች መልኩ ቼክሊስት አዘጋጅቶ ዕቅዱ በጥብቅ ድስፕሊን መፈፀሙን ያረጋግጣል፤
4. በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ የአፈፃፀም ችግሮች ሲኖሩ አስፈላጊውን ማስተካከያና ድጋፍ ይሰጣል፤
5. በሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ አጭር የስራ ግምገማ፣ በወርሃዊና በየሩብ አመቱ በሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል፤
6. የወረዳ ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት።
   - በየሩብ አመቱ ከወረዳ ጽ/ቤት አመራር ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፤
   - በየወሩ ወረዳዎች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ የፅሑፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ-መልስና ድጋፍ ይሰጣል፤
   - በየሳምንቱ ከወረዳዎች ጋር በስልክ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል፤
   - አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት ዕቅድ ለወረዳ ሊግአመራር ኦሬንቴሽን ይሰጣል። በየ3 ወሩ ደግሞ ከጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ ቀበሌዎች ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል ይገመግማል የድጋፍ አቅጣጫንም ያስቀምጣል።
7. በልሳናትና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም በመጽሔት ለሚካሄደው የሊግ አባላት ግንባታ ከብሔራዊ ሊግ ጽ/ቤት የሚተላለፉትን ከዞኑ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፤

8. በልሳናትና በራሪ ፅሁፎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ላይ የታዩ ዝንባሌዎችና አመለካከቶች ወደ ላይኛው አካል እንዲደርስና አስፈላጊው ግብረ መልስ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

9. በየወሩ በዞኑ ካሉት ወረዳዎች ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፤
10. ለብሔራዊ ድርጅት ወ□ቶች ሊግ ጽ/ቤት በ2 ሳምንት የስራ እንፎርሜሽን መስጠት፣ በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፣ በዚህም የግምገማ እና ሂስ ግለሂስ ተደርጎ ማህደር ይሞላል፤
11. የዞኑ ሁለተኛ ሰው ሆኖ የተመደበ ሰው ለዞኑ ወ□ቶች ሊግ ጽ/ቤት ሀላፊ ይሆናል፤
12. ይህ የአሰራር መመሪያ እንደ የብሔራዊ ድርጅት ወ□ቶች ሊጉ ተጨባጭ ሁኔታ በማስተካከል ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፤
13. የዞኑ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለክልሉ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

-----------------------------////---------------------------